08

5ኛ ዓመት ቁጥር 50 5th year №. 50	ባህር ዳር ሀምሌ 30 ቀን 1992 ዓ.ም. Bahir Dar 6th JAugust 2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKER HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 0.90	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 p.O.BOX

ማ ው ጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 50/1992 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ገጽ 2	Proclamation No 50/2000 A proclamation to Amend The Proclamatiom that provides for the financial Administration of the Amhara National Regional State. Page 2

አዋጅ ቁጥር 50 /1992
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደርን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 18/1989 በድጋሚ ማሻሻል በማስፈለጉ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን የማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 50/1992 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ማሻሻያ**

PROCLAMATION NO. 50/2000

A PROCLAMATION TO AMEND THE PROCLAMATIOM THAT PROVIDE THE FINANCIAL ADMINISTRATION OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

WHERE AS, it has become necessary to amend proclamation nº 18/1997 that provides for the financial administration of the Amhara National Regional State;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub article 3/1 of article 49 of the constitution of the region the council of the Amhara National Regional State is here by proclaimed as follows.

1. Short Title

This proclamation may be cited as "A proclamation to amend the proclamation that provides for the financial administration of the Amhara National Regional State No 50/2000."

2. Amendment

"የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 እንደሚከተለው በድጋሚ ተሻሽሏል።

1. የአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሻሽሎ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጽ አንድና ሁለት ተተክቷል። የቀጣዩም ንዑስ አንቀጽ ቅደም ተከተል በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል።
   1. የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ከቢሮው በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከማናቸውም ግብር በዚሁ ላይ ከሚከፈል ወይም ከተከፈለ ወለድ ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል።
   2. የቢሮ ኃላፊው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት በማንኛውም ግብር ላይ ከተጣለ መቀጫ በዚሁ ላይ የሚከፈልን ወይም የተከፈለን ወለድ ጭምር ምህረት ሊያደርግ ይችላል።

2. የአንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተሻሽሏል።
   1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 28 የተመለከተው እንደዚሁም ቢሮው ስለጉዳዩ የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ እና ወጪ ሳይደረግ ወይም ሥራ ላይ ሳይውል የቀረ ሂሳብ ሁሉ ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ ለቢሮው የትሬዥሪ ሂሳብ ፈሰስ ይደረጋል።
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ በገቢው መጠቀም እንዲችል የተፈቀደለት መሥሪያ ቤት ከወጪ ቀሪ እና የእርዳታና ብድር ሂሳብ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ሥራ ላይ መዋሉ ሊቀጥል ይችላል።

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከዛሬ ሀምሌ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር

ሀምሌ 30 ቀን 1992 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት

Proclamation No 18/1997 that provides for the financial administration of the amhara national regional state is here by amended for the 2nd time as follows.

1. Sub article 1 of article 9 is here by amended and substituted by the following sub article 1&2 and there by the consecutive sub article is adjusted in accordance with its sequential order.
   1. The executive committee of the Region believing that there is a good cause and upon the recommendation of the Bureau, may permit any tax including any interest paid or payable on it
   2. The head of the Bureau believing that there is good cause upon the directives issued by the executive committee may remit penalty of any tax including any interest paid or payable on it.

2. Sub article 1 and 2 of Article 28 is here by amended by the following sub article 1 and 2
   1. With out prejudice to article 27 &28 of this proclamation and subject to directives issued by the bureau the unspent balance of an appropriation granted for fiscal year shall lapse and be credited to the treasury Account of the bureau.
   2. Not with standing the provision of sub article 1 of this article, unspent balance of the office permitted to use its revenue up on the regulation issued by the executive committee and grants and loans shall be retained in the consolidated fund for a continual use as may be necessary.

3. Effective Date

This proclamation shall enter into force as of the date of 6 th August 2000.

Done at Bahir Dar

This 6th Day of Aug. 2000

The Council Of The Amhara National Regional State.